# አስፈላጊ ትምህርቶች ለብዙሀኑ ህዝብ

**አዘጋጅ:-**

ሼ/አብዱል አዚዝ ብኑ ባዝ

**ተርጓሚና አሳታሚ:-**

እስላማዊ ዳዕዋና ዕውቀት ማህበር

የመ. ሣ. ቁ 70425
ስልክ 71-32-07

ሁለተኛ እትም 1997

(6) የአማርኛ ትርጉም መብት የተጠበቀ ነው

بسم الله الرحمن الرحيم

## አንደኛ ትምህርት

ፋቲሐ (የመክፈቻይቱ) ምዕራፍ ወምር ከአል ዙልዚላህ (የእንቅጥቃጤው) ምዕራፍ ከሚባለው ጀምሮ እስከ አልናስ (የሰዎች ምዕራፍ) ድረስ ካሉት አጫጭር ምዕራፎች የተቻለውን ያህል ንባባቸውን በማስተካከልና በቃል በማስጠናት እንዲሁም ትርጉሙን ማወቅ ግዴታ የሆነውን አብራርቶ ማስረዳት::

## ሁለተኛ ትምህርት

ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩንና ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን መመስከር፡ ይኸውም ከአንድ አላህ በስተቀር ሊያመልኩት የሚገባ ጌታ ስላለመኖሩና ነቢዩ ሙሐመድ (ሰዐወ) የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን ከነትርጉሙ እንዲሁም የላኢላህ ኢላሏህን ቅድመ ሁኔታዎችን (ሹሩጦችን) ከማብራራት ጋር ማስተማር ነው::

ትርጉሙም:- ላኢላህ የሚባለው ከአላህ ሌላ አምላክ እንደሌለ የሚያሳይ አሉታዊ ቃል ሲሆን፥ ኢለሏህ የሚለው ደግሞ አምልኮን ለአንድ አላህ ብቻ የሚያረጋግጥ አውንታዊ ቃል ነው:: የላኢላህ ኢልለሏህ ቅድመ ሁኔታዎች (ሹሩጦች) የሚከተሉት ናቸው::

1. ለአለማወቅ ተጻራሪ የሆነ ዕውቀት፥
2. ምንም ጥርጣሬ የሌለበት እርግጠኝነት፥
3. ማጋራት ያልተወመረበት ፍጹምነት፥
4. ውሸት የሌለበት እውነተኛነት፥
5. ጥላቻ የሌለበት ውዴታ፥
6. ቸልታ የሌለበት መታዘዝ፥
7. ተቃውሞ የሌለበት መቀበል፥
8. ከአላህ ሌላ ባለ አማልክት በሙሉ መካድ ናቸው::

እነዚህንም ቅድመ ሁኔታዎች በዚህ መንገድ መግለጽ ይቻላል:: ስውቀት: እርግጠኝነት፥ ፍፁምነት፥ እውነተኛነት ከውዴታና ከመቀበል ታዛዥነት ስምንተኛው ደግሞ ከአላህ ሌላ የተመለኩትን ነገሮች መካድ ነው::

## ሦስተኛ እምህርት

የእምነት መሠረቶች ስድስት ናቸው:: እነሱም በአላህ ማመን፥ በመላእክቶች: በመጽሐፍቶች: በመልክተኞች፥ በመጨረሻው ቀንና በቀደር (ደግም ሆነ መጥፎ) በአላህ (ጥራትና ልዕልና ለሱ ይሁንና) ውሳኔና ዕውቀት ነው ብሎ ማመን ናቸው::

## አራተኛ ትምህርት

የተውሂድ (አላህን እንድ የማድረግ) ክፍሎች ሦስት ናቸው:: እነሱም የጌትነት አንድነት: የአምላክነት አንድነት፥ የስሞችና የባህሪያት አንድነት ናቸው::

የሽርክ (የማጋራት) ክፍሎችም ሦስት ናቸው:: ትልቁ ማጋራት፥ ትንሹ ማጋራትና ድብቁ ማጋራት ናቸው:: ትልቁ ማጋራት የተግባርን ከበረትና በገሀነም እሳት ውስጥ መዘውተርን ያስከትላል:: አላህ እንዲህ አለ:-

وَلَوْ أَشْرَكُوا لَحَبِطَ عَنْهُم مَّا كَانُوا يَعْمَلُونَ ﴿٨٨﴾

«ቢያጋሩም ኖሮ ይሰሩት የነበሩት ከነሱ በታበሰ ነበር::»[1]

---

(1) አል አንዓም : 88

**በሌላም አንቀጽ**

مَا كَانَ لِلْمُشْرِكِينَ أَن يَعْمُرُوا مَسَٰجِدَ ٱللَّهِ شَٰهِدِينَ عَلَىٰٓ أَنفُسِهِم بِٱلْكُفْرِ ۚ أُو۟لَٰٓئِكَ حَبِطَتْ أَعْمَٰلُهُمْ وَفِى ٱلنَّارِ هُمْ خَٰلِدُونَ ﴿١٧﴾

*«ለከሃዲዎች በነፍሶቻቸው ላይ በክህደት የሚመሰክሩ ሆነው ያላህን መስጊዶች ሊሰሩ አይገባቸውም። እነዚያ ስራዎቻቸው ተበላሹ፥ እነሱም በእሳት ውስጥ ዘውታሪዎች ናቸው[1]።»*

በዚህም ላይ የሞተ ሰው በምንም ዓይነት አይማርም ገነትም ለሱ እርም ናት አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ አለ፡

إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَغْفِرُ أَن يُشْرَكَ بِهِۦ وَيَغْفِرُ مَا دُونَ ذَٰلِكَ لِمَن يَشَآءُ ۚ

*«አላህ በእርሱ ማጋራትን በፍጹም አይምርም። ከዚህም ሌላ ያለውን ለሚሻው ይምራል[2]።»*

አላህ እንዲህ ይላል፡ إِنَّهُۥ مَن يُشْرِكْ بِٱللَّهِ فَقَدْ حَرَّمَ ٱللَّهُ عَلَيْهِ ٱلْجَنَّةَ وَمَأْوَىٰهُ ٱلنَّارُ ۖ وَمَا لِلظَّٰلِمِينَ مِنْ أَنصَارٍ ﴿٧٢﴾

*«እነሆ በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በርሱ ገነትን በእርግጥ እርም አደረገ። መኖሪያቸውም እሳት ናት። በደዮች ምንም ረዳቶች ላቸውም[3]።»*

---

(1) አል ተውባህ 17

(2) አል ኒሳእ 48

(3) አል ማኢዳህ 72

በዚህ ክፍል ከሚጠቃለሉት መካከል ሙታንንና ጣኦታትን መጥራት በነሱ መመጀን በነሱ መማል ለነሱ ማረድና ሌሎችም ይገኙበታል::

ትንሹ ማጋራት ማለት ደግሞ በቁርአን ወይም በሐዲስ÷ ማጋራት (ሽርክ) ተብሎ ተነግሮ ግን ከትልቁ የማጋራት ዓይነት ያልሆነ ነው:: ለምሳሌ አንድ ነገር ሲፈጸም ለይዩልኝ:: መፈጸም ከአላህ ሌላ ባለ ነገር መማል÷ አላህና እገሌ ካሉ ማለትና የመሳሰሉት ናቸው::

ነቢዩ ሙሐመድ (ሰዐወ) እንዲህ አሉ፡

( أخوف ما أخاف عليكم الشرك الأصغر ) فسئل عنه فقال الرياء

"ለእናንተ ከምፈራላችሁ ሁሉ የምፈራው ትንሹን ማጋራት ነው:: ብለው ሲናገሩ እሱ ምንድነው በማለት ተጠይቀው ሲመልሱ:: ለይዩልኝ መሥራት ነው ብለዋል:: ይህን ሐዲስ በጥሩ የዘገባ ሰንሰለት ኢማሙ አህመድ÷ ጦበራኒና በይሐቂ ሙሐመድ ብኑ ለቢድ የተባሉትን ሰሃባ ጠቅሰው ዘግበውታል:: ጠበራኒ በሌላ የዘገባ ሰንሰለት እኚህ ሰሃባ ከራ ዐ ብን ከዲጅ የሰሙትን ብለው እንደሚከተለው አቅርበውታል::

( من حلف بشيئ دون الله فقد أشرك )

"ከአላህ በስተቀር ባለ ነገር የማለ ሰው በእርግጥ አጋራ"

አቡዳውድና ቲርሚዚ ደግሞ ከዑመር ኢብነል አልኸጣብ በትክክለኛ የዘገባ ሰንሰለት የሚከተለውን ሀዲስ ዘግበዋል::

( من حلف بغير الله فقد كفر أو أشرك )

"ከአላህ ሌላ ባለ ነገር የማለ በእርግጥ አላህን ካደ ወይም በአላህ አጋራ"

ከሁዘይፍህ አልየማኒ አቡዳውድ በትክክለኛ የሐዲስ ሰንሰለት የዘገቡት ደግሞ፡

( لا تقولوا ما شاء الله وشاء فلان، ولكن قولوا ماشاء الله ثم شاء فلان)

"አላህና እገሌ ካሹ አትበሉ እንግዲያውስ አላህ ካሻ ከዚያም እገሌ ከሻ፣ በሉ" የሚል ነው::

ይህ ክፍል ሽርክ ከእምነት መውጣትንም ሆነ በእሣት ውስጥ መዘውተርን አያስከትልም:: ግን ግደታ የሆነውን የተውሂድ ሙሉዕነት ይቃረናል (ይጻረራል)::

ሶስተኛው ክፍል የድብቁ ማጋራት ነው፥ ማስረጃው ተከታዩ የነቢዩችን (ሰዐወ) ቃል ነው::

( ألا أخبر كم بما هو أخوف عليكم عندى مـــن المسيح الدجال؟ " قالوا : بلى يارسو اللّله ؟ قال " الشرك الخفــى ... يقوم الرجل فيصلى فيزين صلاته ، لما يرى من نظر الرجل إليه. )

"አዋጅ ከደጃል ይበልጥ የምፈራላችሁ ነገር ምን እንደሆነ ልንገራችሁ ሲሏቸው እሺ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ይንገሩን አሉዋቸው: "ድብቁ ማጋራት ነው አሉ:: እሱም ሰውየው ይቆምና ይሰግዳል፥ ሰላቱን ያሳምራል፥ ሰውየው ወደሱ መመልከቱን ስለአየ" (ኢማሙ አህመድ የዘገቡት ሐዲስ ነው)

ማጋራትን (ሽርክን) ለሁለት ብቻ መክፈልም ይቻላል:: ይኸውም በትልቅ፥ በትንሽና ድብቅ የሚለው ግን ሁለቱንም የሚያጠቃልል ይሆናል:: በትልቁም ውስጥ እንደ መናፍቃን ማጋራት አይነት ይገኝበታል::

እነሱ መጥፎ እምነታቸውን ደብቀው እስልምናውን ለይዩልንና ለህይወታቸው በመፍራት ከአንገት በላይ ያስመስላሉ:: እንደዚሁም ድብቅ ማጋራትን በትንሹም ማጋራት ውስጥ ይገኛል:: እሱም ባሳለፍነው ሐዲስ ውስጥ እንደተጠቀሰው ለመታየት የተፈጸመን የሚመስል ነው::

## አምስተኛ ትምህርት

የእስልምና ማዕዘናት አምስት ናቸው። እነሱም:

1. ከአላህ ሌላ አምላክ አለመኖሩንና ነቢዩ ሙሐመድ (ሰዐወ) ?አላህ (ሱወ) መልዕክተኛ ናቸው ብሎ በአንደበቱ መመስከር÷
2. ሰላትን መስገድ÷
3. ዘካትን መስጠት፥
4. የረመዳንን ወር መጾም
5. መስፈሪቱን ያሟላ ሰው የተከበረውን የአላህ (ሱወ) ቤት ሄዶ መጎብኘት (የሐጅን ፀሎት ማድረስ) ናቸው።

## ስድስተኛ ትምህርት

ስለ ሰላት ቅድመ ዝግጅቶች (ሸርጦች) እነሱም ዘጠኝ ናቸው።

1. ሙስሊም መሆን÷
2. የአዕምሮ ጤናማነት÷
3. ጠቃሚንና ጎጂን ጥሩና መጥፎውን ለይቶ የማወቅ ዕድሜ መድረስ (አልተምይዝ)
4. ትልቁና ትንሹን ሐደስ ማስወገድ፥[1]
5. ነጃሳን ነገር ማስወገድ፥
6. ሀፍረተ ገላን መሸፈን፥
7. የሚሰገደው ሰላት ጊዜ መግባት
8. ፊትን ወደ ካእባ (ቂብላ) መዞርና
9. ኒያ (ማሰብ) ናቸው

---

(1) ትልቁ ሐደስ ማለትሙሉ ሰውነት መታጠብ የሚያስፈልግ ትንሽ ሐደስ ማለት ውዱእ የሚያስፈልግ ማለት ነው

## ሰባተኛ ትምህርት

የሰላት ማዕዘናት አሥራ አራት ናቸው። እነሱም:-

1. ችሎታ ያለው ሰው መቆም፥
2. የመግቢያ ተክቢራ (አሏሁ አክበር) ማለት፥
3. ፋቲሐን ማንበብ፥
4. ማጎንበስ (ሩኩዕ)፥
5. ከአጎንበሱበት ቀጥ ብሎ መቆም፥
6. በሰባት የሰውነት አካላት ሱጁድ ማድረግ፥ (ከመሬት ላይ ግንባርን ማሳረፍ)፥
7. ከእሱም መነሳት፥
8. በሁለት ሱጁዶች መካከል ለተወሰነ ጊዜ መቀመጥ፥
9. በማንኛውም የሰላት ተግባራትና እንቅስቃሴ ውስጥ መረጋጋት፥
10. በየማዕዘናቱ መካከል ያሉትን ቅደም ተከተል መጠበቅ፥
11. የመጨረሻውን አተህያቱ (ተሸሁድ) ማንበብ፥
12. ለእሱም መቀመጥ፥
13. በነቢዩ ሙሐመድ (ሰዐወ) ላይ ሰላት ማውረድና
14. በሁለቱም ጎን ሰላምታ (አሰላሙ አለይኩም ወራህመቱላህ) ማለት ናቸው።

## ስምንተኛ ትምህርት

የሰላት ዋጅቦች (ግዴታዎች) ስምንት ናቸው[1] እነሱም ከመጀመሪያው ተክቢራ በስተቀር በሰላት ውስጥ ያሉት ተክቢራዎች በሙሉ፥ የሚያሰግድ ሰው (ኢማም) ወይም ብቻውን ሰጋጅ ሰሚ አሏሁ ሊመንሀሚዳህ (አላህ አመስጋኙን ሰሚ ነው) ማለት፥ የሚሰግዱት ሁሉ ረብበና ወለከልሀምድ (ጌታችን ሆይ! ምስጋና ለአንተ ይሁን) ማለት፥ ሲያጎነብስ (ሩኩዕ ሲያደርግ) ሱብሀነረቢያል አዚም (ታላቁ ጌታዬ ጥራትና ልዕልና ይገባው) ማለት፣ መሬት ላይ ሲደፋ (ሱጁድ ሲያደርጉ) ሱብሐና ረቢያል አዕላ (የበላዩ (ሀያሉ) ጌታ ጥራትና ልዕልና ይገባው) ማለት በሁለቱ ሱጁዶች መካከል ረቢግፊርሊ ብሉ (ጌታዬ ማረኝ) የሚጀምረውን ፀሎት ማድረግ የመጀመሪያውን ተሸሁድና (አተሀያቱ) ለሱም መቀመጥ ናቸው።

## ዘጠነኛ ህምህርት

የተሸሁድ (አተሂያቱ) ዝርዝር እሱም:-

( التحيات لله والصلوات والطيبــات السلام عليك أيهـا النبى ورحمةً اللّه وبركاته ، السلام علنـا وعلى عباد اللّه الصالحين، أشــهد أن لا إله ألا اللّه ، وأشهد أن محمدا عبده ورسوله، اللهم صلى على محمد وعلى الٓ محمد كما صليت على إبراهيم وعلى آل إبراهيم إنك حميد مجيد، وبارك على محمد وعلى اَل محمد كما باركت على إبراهيم وعلى آل إبراهيم إنك حميد مجيد .)

"አታሂያቱ ሊላሂ ወሰለዋቱ ወጠይባቱ አሰላሙ አለይካ አዩሀን ነቢዩ

(1) በዚህ መፅሐፍ ውስጥ የተመለከቱት የሰላት ህግጋት (እህካም) በሙሉ በሀንበሊ መዝሀብ መሠረት የቀረቡ መሆኑን አንባቢያን ልብ ሊሉት ይገባል።

ወረህመቱላሂ ወበረካቱሁ አስላሙ አለይና ወአላ ኢባዲላሂ አሷሊሂን አሽሐዱ አንላ ኢላሀ ኢለሏሁ ወአሽሀዱ አነ ሙሐመደን አብዱሁ ወረሱሉሁ። አሏሁመ ሰሊ አላ ሙሐመዲን ወዓላ አሊ ሙሐመዲን ከማሰሌይተ አላ ኢብራሂመ ወዓላ አሊ ኢብራሂመ እነከ ሐሚዱን መጂድ ወባሪክ ዓላ ሙሐመዲን ወአላ አሊ ሙሐመዲን ከማባረክተ ዓላ ኢብራሂመ ወዓላ አሊ ኢብራሂመ ኢነከ ሐሚዱን መጂድ"

ክብሮች ለአንድ አላህ ብቻ ናቸው። ፀሎቶችና መልካም ነገሮችም። አንተ ነቢይ ሆይ! የአላህ ሰላምና እዝነት እንደዚሁም በረከቶቹ በአንተ ላይ ይሁን። የአላህ ሰላም ለእኛና ለደጋጎች የአላህ አገልጋዮች ይሁን። ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ። መሐመድ የአላህ መልዕክተኛና አገልጋይ እንደሆኑ እመሰክራለሁ።

አላህ! ጌታዬ ሆይ በነቢያችን ሙሐመድና ቤተሰቦቻቸው ላይ የአክብሮት ሰላት (ረህመት) አውርድ በነቢዩ እብራሂምና በቤተሰቦቹ ላይ እንዳወረድከው ሁሉ። አንተ በጣም ምስጉንና በጣም ቅዱስ ነህና በነቢያችን ሙሐመድና በቤተሰቦቹ ላይ በረከት አውርድ በነቢዩ እብራሂምና በቤሰቦቹ ላይ እንዳወረድከው ሁሉ። አንተ በጣም ምስጉንና በጣም ቅዱስ ነህና።

ከዚያም በመጨረሻም ቁጭታ ከገሐነምና ከቀብር ቅጣት በሕይወትም ሳለ ሆነ ከሕይወት ሕልፈት በኋላ ከመቸገርና ከደጃል ችግር (ፈተና) በአላህ ይጠበቅ። ከዚያም ከጸሎት (ዱዓእ) ዓይነቶች የመረጠውን ያድርግ። በተለይ ከነቢዩ (ሰዐወ) የተሰማውን ከእነሱም:-

( اللهم اعنى على نكرك وشكرك وحسن عبادتك، اللهم إنى ظلمت نفسى ظلما كثيرا ولا يغفر الذنوب إلا أنت فاغفرلى مغفرة من عنك وإرحمنى إنك أنت الغفور الرحيم )

አልላሁመ አኢኒ ዐላ ዚክሪከ ወሹክሪከ ወሑስኒ ኢባደቲካ አልላሁመ አኢኒ ዘለምቱ ነፍሲ ዙልመን ከሲራን ወላያግፍሩ አልዙኑበ ኢሏ አንተ ፈግፊርሊ መግፊረተን ሚን ዒንዲከ ወርሐምኒ ኢነከ አንተልገፉሩ ረሂም።

ትርጉሙም፡ "አላህ ሆይ! በውዳሴህ በምሥጋናህና በመልካም ሁኔታ እንዳመልክህ አግዘኝ። አላህ ሆይ! ራሴን በብዙ በድያለሁና ካንተ በስተቀር ኃጢአትን የሚምር ስለሌለ ካንተ ዘንድ የሆነ ምህረት አድርግልኝ፣ እዘንልኝ አንተ በጣም መሃሪና አዛኝ ነህና።

## አስረኛ ትምህርት

<u>ስለ ሰላት ሱናዎች</u> ከእነሱም፦

1. የመክፈቻ ፀሎት ማንበብ፥
2. ሲቆም የቀኝ እጁን መዳፍ በግራ እጁ ላይ በማድረግ ከደረቱ ላይ ማስቀመጥ፥
3. የእጆቹ ጣት የተጠጋጉ ሲሆኑ ሁለቱንም እጆች እትከሻ ወይም እጆሮ ድረስ፥

    1ኛ. በመጀመሪያው ተክቢራ

    2ኛ. ሲያጎነብስ (ሩኩዕ ሲያደርግ)

    3ኛ. ተመልሰው ቀጥ ሲሉና

    4ኛ. ከመጀመሪያው ተሸሁድ ለሶስተኛው ረከዓ ሲነሱ ማንሳት

4. በማጎንበስ ጊዜም ሆነ በመሬት ላይ በመደፋት ጊዜ ከአንድ ጊዜ በላይ በመጨመር ተስቢህ (አላህን ማጥራት)፥
5. በሁለቱ ሱጁዶች መካከል ከአንድ ጊዜ በላይ ምህረትን መለመን፥
6. ሲያጎነብሱ እራስን በጀርባ ትክክል ማድረግ፥
7. በመሬት ላይ ሲደፉ (በሱጁድ) ጡንቻዎችን ከጎኖቹ ሆድን ከጭኖቹ ማራቅ፥
8. ሱጁድ ሲደረግ ክንዶችን ከመሬት ማንሳት (ማራቅ)፥

9. በመጀመሪያው ቁጭታና (ተሸሁድ) በሁለቱ ሱጁዶች መካከል ባለው ጊዜ የቀኝ እግሩን ጣት ተክሎ በግራ እግሩ ላይ መቀመጥ፥

10. በመጨረሻ ቁጭታ (ተሸሁድ) ጊዜ የቀኝ እግሩን ጣት በመትከል መቀመጫን መሬት ማስነካት፥

11. በመጀመሪያው ቁጭታ (ተሸሁድ) ሰላትንና ረድኢትን ለነቢዩ ሙሐመድና ለቤተሰቦቻቸው፣ ለነቢዩ ኢብራሂምና ለቤተሰቦቻቸው መለመን፥

12. በመጨረሻው ቁጭታ (ተሸሁድ) ፀሎት ማድረግ፥

13. በሱብሂ ሰላት በሁለቱም ረከዓዎች በመግሪብና በኢሻ በሁለቶች የመጀመሪያ ረከዓዎች ድምጽን ከፍ አድርጎ ቁርአን ማንበብ፥

14. በዙሁርና በዐስር በሁሉም ረከዓዎች በመግሪብ በሶስተኛውና በኢሻ በሁለቶች የመጨረሻ ረከዓዎች ድምጽን ዝቅ አድርጎ ሳያሰሙ ማንበብና

15. ከፋቲሐ ሌላ በተጨማሪ የቁርአን ምዕራፍ (አንቀፅ) ማንበብ ነው ይህም ሌሎችንም በዚህ መጽሐፍ ያልጠቀስናቸውን የሰላት ሱናዎች ከመጨመር ጋር ነው።

## አስራ አንደኛ ትምህርት

ሰላትን የሚያበላሹ ነገሮች ስምንት ናቸው። እነሱም:

1. ከማወቅና ከማስታወስ ጋር መናገር: የረሳ ወይም ያላወቀ ግን በመናገሩ ሰላቱ አይበላሽበትም።

2. ሳቅ 3. መብላት 4. መጠጣት 5. ሐፍረተ ገላ መገለጥ 6. ከካዕባ (ቂብላ) አቅጣጫ በብዙ መዞር 7. በሰላት ውስጥ በተከታታይ ብዙ እንቅስቃሴ ማድረግ 8. የውዱእ መበላሸት (መፍረስ)

## አስራ ሁለተኛ ትምህርት

የውዱእ ቅድመ ሁኔታዎች (ሸርጦች) አስር ናቸው፡፡ እነሱም፡- ሙስሊም መሆን፡ የአዕምሮ ጤናማነት፥ ጠቃሚንና ጎጂን ቀኙና መጥፎን ለይቶ የማወቅ ዕድሜ መድረስ፥ መነየት፥ ውድእ እስከሚያበቃ ሳለማቋረጥ መወሰን፥ ውዱእን የሚያስገድዱ ነገሮች መቋረጥ፣ አስቀድሞ በውሃ ወይም በድንጋይ (በመሳሰሉት) የሽንትንና የሰገራን መውጫውን ማጠብ (ማበስ)፥ ውሀው ንፁህ መሆንና ሊጠቀምበት የተፈቀደ መሆን፥ ውሀው ወደ ሰውነት እንዳይዳረስ (እንዳይዘልቅ) የሚከለክሉ ነገሮችን ማስወገድና ሁልጊዜ የማይለቅ የውዱእ ማጥ ያ ችግር ያለበት ሰው ሊሰግደው ለሚፈልገው ሰላት ወቅት መግባት ናቸው፡፡

## አስራ ሶስተኛ ትምህርት

የውዱእ ግዴታዎች ስድስት ናቸው፡፡ እነሱም ትን መታጠብ፥ ሲሆን አፍን . መጉመጥመጥና በአፍንጫ ውሀን ማስገባትም ከዚሁ ጋር፥ ይጠቃለላል[1]. ሁለቱን እጆች ከክርኖች ጋር ማጠብ፥ ሁሉን የራስ ፀጉርና ጆሮዎችንም ሙምር ማበስ፡፡ ሁለቱን እግሮችን ከቁርጭምጭሚቶች ጋር ማጠብ፡፡ የተጠቀሱትን የውዱእ አካሎች ቅደም ተከተላቸውን መጠበቅና ማለጣጠቅ (ማከ:ታተል) ናቸው፡፡

## አስራ አራተኛ ትምህርት

ውዱእን የሚያበላሹ ነገሮች ስድስት ናቸው፡፡ እነሱም፡

ከሁለቱ የቆሻሻ መውጫ ብልቶች የወጣ ሁሉ፥ ከሰውነት የወጣ ነጃሳ ነገር በእንቅልፍም ሆነ በሌላ ነገር አዕምሮ መሳት፥ ሁለቱን የእፍረት ገላዎች ያለ

(1) መጉመጥመጥና ውሀን በአፍንጫ ውስጥ ማስገባትን ከዋጅብ (ግዴታ) ውስጥ መቁጠር በሐንበሊ መዝሀብ መሠረት ነው፡፡

ምንም ከለላ በእጅ መንካት፣ የግመል ሥጋ መብላት[1]፣ አላህ ይጠብቀንና ከእስልምና መውጣት።

<u>አንገብጋቢ ማሳሰቢያ</u>፡ እራሳን ማጠብ በትክክለኛ አስተያየት ውዱእ አያጠፉም። ይህም የብዙሀኑ አሊሞች (ሙሁሮች) አስተያየት ነው። ለማበላሸቱ ማስረጃ ስላልተገኘለት ነው። ሆኖም አጣቢው የእራሳውን ገላ ያለ ምንም ግርዶ መንካት የለበትም። እንደዚሁ ከአሊሞች በጣም ትክክለኛ በሆነው አቋም ሴትና ወንድ መነካካት በስሜትም ሆነ ያለስሜት ከብልት ፈሳሽ ነገር ካልወጣ በስተቀር አይበላሽም። ምክንያቱም ነቢዩ ሙሐመድ (ሰዐወ) አንዲቱን ሚስታቸውን ስመው ውዱእ ሳያድሱ ሰግደዋልና በማኢደህና በኒሳእ ምዕራፎች ውስጥ

أَوْ لَٰمَسْتُمُ ٱلنِّسَآءَ

(ወይም ሴቶችን ነካችሁ) ያለው ከአሊሞች ከፍተኛ ድጋፍ ያለው በዚህ የታሻው ግብረ ሥጋ ግንኙነት ነው ይህም አባባል የአብደላህ ኢብን አባስና የሌሎች የብዙ ሰዎች አስተያየት ነው[2]።

<u>አስራ አምስተኛ ትምህርት</u>

ለማንኛውም ሙስሊም እንዲላበሳቸው ስለተደነገጉት ባህሪዎችና ሥነ ምግባሮች ከእነዚህም መካከል እውነተኛነት፣ ታማኝነት፣ ጥብቅነት፣ እፍረት (ሐያዕ) ጀግንነት፣ ቸርነት፣ በቃል መሙላት፣ አላህ ከከለከላቸው ነገሮች ሁሉ መራቅ ጉርብትናን ማሳመር፣ በተቻለው አቅም ችግረኛን መርዳትና ሌሎችም በቁርአንና በሐዲስ የተደነገጉ ባህሪያቶች ይገኙበታል።

---

(1) የግመል ሥጋ ውዱእ ያበላሻል የተባለው በሐንበሊ መዝሐብ ነው።

(2) የሴትና ወንድ በስሜት መነካካት ውዱእን እንደሚያበላሽ በሀንበሊም መዝሀብ ተገልጧል።

## አስራ ስድስተኛ ትምህርት

ስለ እስላማዊ ስርአቶች ከእነዚህም መካከል ሰላምተኝነት፥ ፈገግተኝነት፣ በቀኝ መጠጣትና መብላት፥ ወደ መስጊድ ወይም ወደ ቤት ሲገቡና ሲወጡ እና መንገድ ሲሄዱ እንዲተገበሩ የተደነገጉትን ስረአቶች መጠበቅ ከወላጆች ጋርና ከዘመዶች፥ ከጎረቤቶች ከአዋቂዎችና ከሀፃናቶች ጋር ሊኖር የሚገባውን ስረአት መተግበር ህፃን ሲወለድ እንኳን ደስ ያላችሁ በማለት የደስታ መግለጫ መስጠት፥ ሰው ለሞተበት አላህ ትዕግስቱን ይስጣችሁ በማለት ማጽናናትና ሌሎችም እስላማዊ ስርዓቶችን መጠበቅ::

## አስራ ሰባተኛ ትምህርት

ከማጋራትና ከወንጀሎች ሁሉ መጠንቀቅ ነው:: ከእነዚህም መካከል ሰባቱ የሰው ልጆችን አጥ ፊዎች በመባል የታወቁ ከባድ ኃጢአቶች ይገኙበታል:: እነሱም በአላህ ማጋራት፥ ድግምት፥ አላህ ክልክል ያደረጋትን ሕይወት ያለ አግባብ ማጥፋት፥ የየቲሞችን (አባት የሞተባቸውን) ገንዘብ መብላት ወለድ (አራጣ) መብላት በጦርነት ቀን ከተሰለፉ በኋላ መሸሽ ጥብቅ (ንፁህ) የሆኑ ሴቶቹ በዝሙት መስደብ (መወንጀል)::

ከዚህም በተጨማሪ የወላጆችን ሐቅ መርገጥ፥ ዝምድናን መቁረጥ፣ የሐሰት መስክር መስጠት፥ የሐሰት መሐላ፣ ጎረቤትን ማስቸገር፥ ሰዎችን በደም በገንዘብ በገመና መበደልና ማስቸገር ሌሎችም አላህ ወይም ነቢዩ (ሰዐወ) የከለከሏቸው ሁሉ ነገሮች ይገኙበታል::

## አስራ ስምንተኛ ትምህር፡

እሬሳን መሸኘት በእሱ ላይ መስገድ ዝርዝሩ የሚከተለው ነው፡

የራስ አዘገጃጀት፡-

1 መሞቱ ሲረጋገጥ አይኖቹ ይገጠማሉ መንገጭሎቹ ይገጣጠማሉ::

2. እራሳው ሲታጠብ እፍረተ ገላው ይሸፈናል:: ቀጥሎም ትንሽ ከፍ ይደረግና የሚወጣ ነገር ካለ ይወጣለት ዘንድ ሆዱ በቀስታ ይጨመቃል ከዚያ ቀጥሉ አጣቢው በእጁ ላይ ጨርቅ መሳይ ነገር ጠቅልሉ እስትንጃ ያደርግለታል:: ከዚያም የሰላት ውዱእን የመሰለ ያደርግለታል:: ቀጥሎም እራሱንና ጽሙ በውሀና በቁርቁራ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ነገር ያጥበዋል ከዚያ ቀኝ ጎኑን ያጥባል፡ አስከትሉም ግራውን እንደዚሁ እያደረገ ለሁለተኛና ለሶስተኛ ጊዜ ያጥበዋል:: በእያንዳንዱ እጥበት ሁሉ እጅን በሆድ ላይ ያስኬዳል (ያሽዋል) የሆነ ነገር ከወጣ ያጥበውና መውጫውን በጥጥ ወይም በሌላ ነገር ይወትፈው:: ይህም ካልገደበው በንፁህ የአፈር ጭቃ ወይም በዘመን አመጣሽ የህክምና ዘዴ ማፈኛ ይዝጋው:: ውዱእ እንደገና ያድርግለት በሶስቱ ባይጸዳ እስከ አምስት እስከ ሰባት ይጨምርበት ከዚያም በጨርቅ ያድርቀው:: በመታጠ ያዎችና በሱጁድ ማድረጊያ ቦታዎች ላይ ሽቶ ያድርግለት:: በመላ አካላቱ ላይ ሽቶ ቢደረግለት ይመረጣል:: ከፈኑን በጭስ ያጥንለት:: ሪዝና ጥፍሩ ረጅም ከሆኑ ይቆረጣሉ ፀጉሩ አይበጠርም፡ ሴት ግን ፀጉሯ ለ3 ተጎንጉኖ ወደ ኋላዋ ይለቀቃል::

3 <u>እራሳን መገነዝ</u>

ወንድ ከሆነ በሶስት ነጫጭ ጨርቆች፣ ቀሚስና ጥምጣም በሌላቸው መገነዙ ይበልጣል:: ተራ በተራ ይጠቀለልበታል:: በቀሚስ በሸርጥና በአንድ ብትን መጠቅለያ ቢገነዝ ምንም አይደል:: ሴት ግን በአምስት ጨርቆች ማለት በቀሚስ በጉፍታ በአንድ ሽርጥና በሁለት መጠቅለያ ጨርቆች ነው የምትገነዘው:: ህፃን ልጅ ከአንድ እስከ

ሦስት በሚሆን ጨርቆች ይገነዛል:: ሴት ሆኖን በቀሚስና በሁለት ጨርቆች ትገነዛለች::

እራሳን ለማጠብ በእሱ ላይም ለመስገድና ለማስቀበር መብት ሚኖ የተናዘዘለት ሰው ነው:: ከዚያም የሚኖ አባት፥ አያት፥ ወራሽ ዘመዶች እንደቅርበታቸው:: ሴትን ለማጠብ ባለመብት የታናዘዘችላት ስትሆን ከዚያም እናት፥ አያት፥ ከዚያም ሴት ዘመዶች እንደቅርበታቸው ደረጃ ባልና ሚስት አንዱ ሌላውን ሊያጥብ ይችላል:: አቡበክር ሲድቅን ያጠቧቸው ባለቤታቸው ነበሩ:: አሊም ባለቤታቸው ፋጡማን አጥበዋል::

5. በሚች ላይ አሰጋገድ እንደሚከተለው ነው:- አራት ጊዜ አላሁ አክበር ይባላል:: ከመጀመሪያ ቀጥሎ ፋቲሐ (የመክፈቻው) ምዕራፍ ይነበባል:: አብሮ ሌላ አጠር ያለ የቁርአን ምዕራፍ ወይም አንድ አንቀጽ ወይም ሁለት አንቀጽ ቢነበብ ጥሩ ነው:: ይህን በተመለከተ አብዱላሂ ኢብን አባስ የዘገቡት ትክክለኛ ሐዲስ ስላለ ነው:: ሁለተኛውን ተክቢራት ከደረገ በኋላ በሰላት (በተሸሁድ) ውስጥ በነቢዩ (ሰዐወ) ስለዋት እንደሚለምን ሁሉ ይለምን (ያውርድ) ሶስተኛውን ተከቢራ ካደረገ በኋላ የሚከተለው ፀሎት ይነበባል::

( اللهم اغفر لحينا وميتنا، وشاهدنا وغائبنا وصغيرنا ، وكبيرنا ، وذكرنا ، وأنثانا ، اللهم من أحييته منا فأحيه على الاسلام ، ومن توفيته منا فتوفه على الايمان ، اللهم اغفر له ، وارحمه ، وعافه ، واعف عنه ، وأكرم نزله ،

(1) ርዝ ማለት በላይኛው ከንፈር ላይ የምበቅል ጠጉር ነው ጽሙ ግን አይነካም

ووسع مدخله ، واغسله بالماء والثلج والبرد ، ونقه من الخطايا ، كما ينقى الثوب الابيض من الدنس ، وأبدله دارا خيرا من داره ، وأهلا خيرا من أهله، وأدخله الجنة ، وأعذه من عذاب القبر ، وعذاب النار ، وافسح له فى قبره ، ونور له فيه ، اللهم لا تحرمنا أجره ، ولا تضلنا بعده . )

"አላሁመ ኢግፊር ሊሐይና ወመይቲና ወሻሂዲና ወጋኢቢና ወሰጊሪና ወከቢሪና ወዘከሪና ወዑንሳና አላሁመ መን አህያይ ተሁ ሚንና ፈአህይሂ አላል ኢስላም ወመን ተወፈይተሁ ሚንና ፈተወፈሁ አለል ኢማን አላሁመ ኢግፊር ለሁ ወግሲልሁ ቢልማኢ ወሰልጂ ወልበረዲ ወነቂሂ ሚናል ዙኑብ ወ ኸጣያ ከማ ዩነቃ አሰውቡል አብየዱ ሚና አልደነሲ ወአብዱልለሁ ዳረን ኸይረን ሚን ዳሪሂ ወአህለን ኸይረን ሚንአህሊሂ ወአድኺልሁ አልጀኑተ ወአኢዝሁ ሚን አዛቢል ቀብሪ ወአዛቢ ንናር ወአፍሲሀለሁ ፊቀብሪሂ ወናዊርለሁ ፊሂ አላሁመ ላተህሪምና አጅረሁ ወላቱዲለና ባዕደሁ::"

<u>ትርጉመም</u>: "አላህ የይ! በሕይወት ያለንንም የሞተንም በቅርብ ያለውንም በሩቅ ያለውንም ትልቆችንንም ትንሾችንንም ወንዶችንንም ሴቶችንንም ማረን:: አላህ ሆይ! ከመካከላችን በሕይወት የምታቆየውን ሰው በእስላም ላይ አቆየው:: ከመካከላችን የምታሳርፈውን በእምነት ላይ እንደሆነ አሳርፈው:: አላህ ሆይ! ምህረት አድርግለት እዘንለትም ጠብቀው ይቅርም በለው መስተንግዶውን አሳምርለት፥ መግቢያውንም አስፋለት ኃጢአቱንም በውሀና በበረዶ እጠብለት ነጭ ልብስ ከቆሻሻ እንደሚፀዳ አፅዳው፥ ከቤቱ የተሻለ ቤት ከቤተሰቡ የተሻለ ቤተሰብ ቀይርለት::

ወደ ገነትም አስገባው፥ ከቀብር ውስጥ ቅጣትና ከእሳትም ቅጣት ጠብቀው:: መቃብሩንም አስፋለት:: አብራለትም:: አላህ ሆይ! ምንዳውን አትንፈገን ከርሱም በኋላ እጣችንን ጥመት አታድርግብን::

ከአራተኛው ተክቢራ በኋላ በቀኝ ጎኑ ብቻ ሰላምታ ይባላል በያንዳንዱ ተክቢራ ጊዜ እጅን ማንሳቱ ይወደዳል:: ሴት ከሆነች ፀሉቱን እንዲህ ብሉ

(اللهم اغفر لها) "አሏሁማ እግ ር ለሃ" ይነበብ፥ ሁለት ከሆኑ (اللهم اغفر لهما) "አሏሁማ እግ ር ለሁማ" በማለት ብዙም ከሆኑ በብዙ (اللهم أغفر لهم) "አሏፊሁማ እግ ́ር ለሁም ተብሎ ይነበብ:: ሟች ህፃን ከሆነ ያለፈውን ትቶ እንዲህ በማለት ዱዓ ይደረግ::

( اللهم اجعله فرطا ونخرا لوالديه، وشفيعا مجابا، اللهم ثقل به موازينهما وأعظم به أجورهما وألحقه بصالح المؤمنين، واجعله في كفالة إبراهيم عليه السلام، وقه برحمتك عذاب الجحيم )

"አላሁመመ ኢጅአልሁ ፈረጣን ወዙክረን ሊዋሊደይሂ ወሸ አን ሙጃበን አላሁመመ ሰቂል ቢሂ መዋዚነሁማ ወዐዚም ቢሂ ዐጅረሁማ ወአልሂቅሁ ብሳሂልና ሙእሚኒን ወጀአልሁ ፊ ከፋለቲ ኢብራሂመ (ሰዐወ) ወቂሂ ቢራህመቲካ አዛብ አልጀሂም::"

<u>ትርጉሙም</u>:- "አላህ ሆይ! ለወላጆቹ በወዲያኛው ሕይወት ደህንነት ቀድሞ ሂዶ የሚያመቻች ቀዳሚ ለችግር ቀን አለኝታ፥ ተሰሚነት ያለው አማላጅ አድርግላቸው:: አላህ ሆይ! የመልካም ሥራቸው ሚዛን ማክበጃ የምንዳቸው ማብዣ አድርገው፥ ከደጋግ ምዕመናን ጋርም አስጠጋው በነቢዩ ኢብራሂም (ሰዐወ) እንክብካቤ ሥር አድርገው፥ በችሮታህም ከገሀነመ እሳት ጠብቀው::

ኢማሙ ለማስገድ ሲቆም ሱናው ሟች ወንድ ከሆነ በራሱ አቅጣጫ ሴት ከሆነች በመሐከል ሰውነቷ አቅጣጫ መቆም ነው:: ወንድና ሴት ከሆኑ ወንድ ወደ ኢማሙ በኩል ሴቷ ወደ ቂብላ በኩል ነው የሚደረገው:: ህፃን ካለ መጀመሪያ ህፃኑ ቀጥሎ ሴቲ ቀጥሎም ህፃኗ ሆነው የሚቀመጡት:: የህፃኑ ራስ በወንድ ራስ አቅጣጫ ሲሆን የሴት መሐል ሰውነት እንደዚሁ በወንዱ ራስ ትይዩ ይሆናል:: እንደዚሁ የህፃኗ ራስ አቅጣጫ የሚሆነው፥ በሴት ራስ አቅጣጫ የህፃኗ መኻከል እወንዱ ራስ አቅጣጫ ነው የሚሆነው የሚሰግዱት

ሰዎች በሙሉ ከኢማሙ በኋላ ይሆናሉ። አንድ ሰው ብቻ ቦታ ካላገኘ በኢማሙ በቀኝ ጎን ይቆማል።

ለአላህ ብቻ ምስጋና ይገባው። ረህመቱ ረድኢቱን በነቢዩና በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ይውረድ።

**ተፈጸመ**

بسم الله الر حمن الر حيم

## تقديم

يسر جمعية الدعوة والثقافة الإسلامية بأديس أبابا أن تقدم لمسلمي إثيوبيا ترجمة هذا الكتاب المهم بعنوان "*الدروس المهمة لعامة الأمة*" لسماحة الشيخ / عبد العزيز بن عبد الله بن باز باللغة الأمهرية وذلك لتعم الفائدة ، كما نشكر كل من ساهم وتعاون مع الجمعية في نشر هذا الكتاب باللغات المحلية في إثيوبيا ، ونسأل الله أن يجازيهم خيرا على خدمة دينه الحنيف إنه ولي ذلك والقادر عليه .

وصلى الله وسلم على نبينا محمد وعلى آله وصحبه أجمعين

جمعية الدعوة والثقافة الإسلامية

أديس أبابا - إثيوبيا

# الدوس المهمة لعامة الامة

تأليف

سماحة الشيخ عبد العزيز بن عبد الله بن باز

الترجمة والنشر

جمعة الدعوة والثقافة الإسلامية

بأديس أبابا

ص. ب : ٧٠٤٢٥

هاتف: ٧١٣٢٠٧

( ٦ ) الطبعة الثانية ١٤١٨هـ - ١٩٩٧م

حقوق الطبع بالأمهرية محفوظة

مطابع الدار الهندسية/القاهرة

تليفون/فاكس : (٢٠٢) ٥٤٠٢٥٩٨